የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሳኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፮

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No.50
ADDIS ABABA ,30th July , 2024

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፶፭/፪ሺ፲፮

የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ........................................ገጽ ፲፭ሺ፯፻፵፬

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፶፭/፪ሺ፲፮

## የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፩፻፫ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፭፻፶፭/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "ሥነ-ልክ" ማለት የአለካክ ሳይንስና ትግበራው ነው፤

## Content

Regulation No.555/2024

Establishment of the Ethiopian Metrology Institute Regulation...............Page 15744

## REGULATION No.555/2024

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE ETHIOPIAN METROLOGY INSTITUTE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 103 of Proclamation No.1263/2022 established to determine the Power and Duties of the Executive Organs.

### 1.Short Title

This Regulation may be cited as the " The Ethiopian Metrology Institute Establishment Regulation No.555/2024".

### 2. Definition

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "Metrology" is the Science of Measurement and its application;

፪/ "ሕጋዊ ሥነ-ልክ" ማለት በሕግ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ልኬትን፣ የልኬት አሃዶችን፣ የመለኪያ መሣሪያዎችን እና የልኬት ዘዴዎችን ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ የሥነ-ልክ ሕግን በሚያስፈጽሙ አካላት የሚከናወን ተግባር ነው፤

፫/ ልኬት" ማለት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የቁስ መጠንን በሳይንሳዊ ሙከራ የማግኘት ሂደት ሲሆን ውጤቱ በተቻለ መጠን ለቁሱ የሚቀርብ ባህርይ ነው፤

፬/ የልኬት አሃድ" ማለት በዓለም አቀፍ በስምምነት የተወሰነና ተቀባይነት ያገኘ እውነተኛ ቁሳዊ መጠን ሲሆን ሌሎች ተመሳሳይነት ያላቸውን ቁሳዊ መጠን በጥምርታ በማነጻጸር በአሃዝ የሚገለጽበት ነው፤

፭/የልኬት እርግጠኛ ያለመሆን" ማለት ጥቅም ላይ በዋለው የልኬት መረጃ መሰረት ለተለኪው የተሰጠ የቁስ መጠን ስብጥር ባህሪን ለማወቅ የሚያስችል ነጋቲቭ ያልሆነ ቁጥር ነው፤

፮/ የመለኪያ ስታንዳርድ" ማለት የአንድን አሃድ ትርጓሜ በተገለጸው የቁስ መጠንና ከተያያዥ የልኬት እርግጠኛ አለመሆንን ዕውን በማድረግ እንደማመሳከሪያ የሚያገለግል ነው፤

፯/ብሔራዊ የመለኪያ ስታንዳርድ" ማለት በብሔራዊ ደረጃ ህጋዊ በሆነ አካል ተቀባይነት ያገኘ ሆኖ የሌሎችን መሰል የመለኪያ ስታንዳርዶችን መጠን ለመወሰን እንደመሰረት የሚያገለግል ነው፤

2/ “Legal Metrology” is a law enforcement practice relating to the verification of measurements, units of measurements, measuring instruments and methods of measurements in accordance with the requirements set forth by law;

3/ "Measurement" is the process of experimenttally obtaining one or more quantity values that can reasonably be attributed to a quantity;

4/ "Measurement Unit" is real scalar quantity, defined and adopted by convention, with which any other quantity of the same kind can be compared to express the ratio of the two quantities as a number;

5/ “Measurement uncertainty” is non-negative parameter characterizing the dispersion of the quantity values being attributed to a measureand, based on the information used;

6/ “Measurement Standard”is realization of the definition of a given quantity, with stated quantity value and associated measurement uncertainty, used as a reference;

7/ “National Measurement Standard” is measurement standard recognized by national authority to serve in a state or economy as the basis for assigning quantity values to other measurement standards for the kind of quantity concerned;

9/3/24 8:19:1

CS CamScanner

፰/ስረት" ማለት በላብራቶሪ ሊወሰኑ ወይም ሊገለጹ የሚችሉ ተፈላጊ ባህሪያትን ይዞ እንደሚገኝ ታስቦና በሳይንስ በተደገፈ መላምት ተመርጦ የሚዘጋጅ ቁስ ነው፤

፱/"ማመሳከሪያ ስረት" ማለት ከተለዩ ባህሪያት አንጻር በደንብ የተዋሃደና የተረጋጋ ስረት ሲሆን ለተፈለገው ልኬት ወይም የተገለጸ ባህሪን ለመመርመር አገልግሎት ብቁ ሆኖ የተዘጋጀ ነው፤

፲/የተመሰከረለት ማመሳከሪያ ስረት" ማለት ትክክለኛ የአሰራር መመሪያ በመጠቀም በህጋዊ አካል በወጣ ሰነድ የተደገፈ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሚፈለገው ባህርይ መጠን ከነተዛማጅ እርግጠኛ-ያለመሆን የተወሰነለትና እና የዕርከን ተዋረድ (ትስስር መጠበቁ የተሰነደለት) የማመሳከሪያ ስረት ነው፤

፲፩/የመለኪያ መሣሪያ" ማለት ብቻውን ወይም አንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ተጨማሪ መሳሪያዎች ጋር በመቀናጀት ለልኬት የሚውል መሣሪያ ነው፤

፲፪/ካሊብሬሽን" ማለት የመለኪያ ወይም የአናሊስ መሳሪያዎችን ትክክለኛነት እና ከትክክለኛነታቸው ጋር በተገናኘ የሚያሳዩትን ባህሪያት ለመወሰን የሚከወን የስነ-ልክ ትግበራ ነው፤

፲፫/የሥነ-ልክ ዕርከን ተዋረድ ትስስር" ማለት የልኬት ውጤት ባህርይ ሲሆን ውጤቱም በተሰነደ ያልተቆራረጠ

8/ "Material" is a substance that is selected and prepared based on a scientifically supported hypothesis, that it has desirable properties that can be determined or defined in a laboratory.

9/ "Reference Material (RM)" is material, sufficiently homogeneous and stable with reference to specified properties, which has been established to be fit for its intended use in measurement or in examination of nominal properties;

10/ "Certified Reference Material (CRM)" is reference material,accompanied by documentation issued by an authoritative body and providing one or more specified property values with associated uncertainties and traceability, using valid procedures;

11/ "Measurement Instrument" is device used for making measurements, alone or in conjunction with one or more supplementary devices;

12/ "Calibration" is the application of metrology to characterize the accuracy and performance of measuring or analysis instruments in relation to their accuracy;

13/ "Metrological traceability" is property of a measurement result whereby the result can be related to a reference

የካሊብሬሽን ሰንሰለት ከማመሳከሪያው ጋር የተዛመደና እያንዳንዱ ካሊብሬሽን ለልኬት እርግጠኛ ያለመሆን የሚያበረክተውን የሚያካትት ነው፤

through a documented unbroken chain of calibrations, each contributing to the measurement uncertainty;

፲፬/ የሳይንስ መሣሪያ" ማለት ለምርምርና ሥርዓት፣ ለትምህርትና ሥልጠና፣ ለጥራት ቁጥጥርና ፍተሻ፣ ለሥነ-ልክ ወይም ለሰው ወይም ለእንስሳት ሕክምና አገልግሎቶች ሥራ ላይ የሚውል መሣሪያ ነው፤

14/ "Scientific Equipment" is a device used for research and development, education and training, quality control and inspection, metrology or diagnosis and treatment of human beings or animals;

፲፭/ የህክምና መሳሪያ" ማለት ህመምን ለመከላከል፣ ለመመርመር፣ ወይም አክሞ ለማዳን ወይም ለሆነ የጤና ጉዳይ የሰው አካል አሰራርን ለማወቅ፣ ለመለካት፣ ወደነበረበት ለመመለስ፣ ለማስተካከል ወይም ለመለወጥ የሚጠቅም መገልገያ፣ እቃ፣ ማሽን ወይም መሳሪያ ነው፤

15/ "Medical Device" is an article, instrument, apparatus or machine that is used in the prevention, diagnosis or treatment of illness or disease, or for detecting, measuring, restoring, correcting or modifying the structure or function of the body for some health purpose;

፲፮/ የቴክኒክ አገልግሎት" ማለት የሳይንስ መሳሪያን የመትከል እና በአምራቹ መስፈርት መሰረት መሆኑን የመፈተሽ፣ ብልሽትን የመለየት፣ የመጠገን፣ የማደስ፣ የማሻሻል ወይም የመንቀል ተግባራትን ማከናወን ነው፤

16/ Technical Service" is performing installation and commissioning, troubleshooting, repairing, maintaining, modifying, or decommissioning works of scientific equipment;

፲፯/ የመሳሪያ ሕይወት ዑደት" ማለት የሳይንስ መሳሪያን ከጽንሰ-ሀሳብ ጀምሮ የማጎልበት፣ የማምረት፣ ገበያ ላይ የማዋል፣ ከመጠቀም እስከ ማስወገድ ባሉ የስራ ዑደቶች የሚከናወኑ ተግባራትና የአመራር ስርዓት ማለት ሲሆን ከተጠቃሚዎች አንፃር በዋናነት የማቀድ፣ የማግኘት፣ የመጠቀምና የማስወገድ ሂደቶችን የሚያካትት ነው፤

17/ "Equipment Life Cycle" is, process and activities and management practices of scientific equipment from conception and development,manufacturing, putting in market, utilization to disposal. From users' perspective planning, acquisition, utilization and disposal are major process contained;

CamScanner

፲፰/ ሚኒስቴር" ማለት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ነው፤

፲፱/ ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳/ማንኛውም በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ይገልጻ

፫.<u>መቋቋም</u>

፩/ የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩቱ" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

፬.<u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ቦታ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

፭.<u>ዓላማ</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ በሥነ ልክ እና በሳይንስ መሳሪያ መስኮች ጥናትና ምርምር በማካሄድ የቴክኖሎጂ ሽግግር አቅም ማሳደግ፣ የስልጠና፣የማማከር እና የቴክኒክ አገልግሎቶችን በመስጠት በንግዱ ዘርፍ የጥራት ተወዳዳሪነትን

18/ "Ministry" means the Ministry of Trade and Regional Integration;

19/ "Person" means a natural or juridical person;

20/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. <u>Establishment</u>

1/ The Ethiopia Metrology Institute (Hereafter referred to as "the Institute") is hereby established as an autonomous Federal Government office having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

4.<u>Head Office</u>

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices anywhere, as may be necessary.

5.<u>Objective</u>

The Institute shall have the following objectives:

1/ To enhance technology transfer capability by conducting research and development on metrology and scientific instruments;to increase quality competitiveness in the business sector, to protect the social and economic benefits of the society and to

ማሳደግ፤ የሕብረተሰቡን የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ማስጠበቅ እና የፈጠራና የምርምር ሥራዎች ጥራት ማሳደግ፤

፪/ ብሔራዊ የመለኪያ ስታንዳርዶችንና የተመሰከረላቸውን የማመሳከሪያ ስረቶች ለመጠበቅ፤ ከዓለም አቀፍ የመለኪያ ስታንዳርድ ጋር ለማመሳከርና ለማሰራጨት የሚያስችል ከዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ሥርዓት ጋር የተጣጣመ ብሔራዊ የአለካክ አሰራር ሥርዓት መዘርጋትና መተግበር፤

፫/ ሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች አገራችን ዘለቄታዊ ተጠቃሚነቷን የሚያረጋግጡ ጉልህ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ አስተዋፆዎችን በማድረግ ከአፍሪካ ቀዳሚ ተቋማት ተርታ ተጠቃሽ መሆን።

፮. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር በማካሄድ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በተለያዩ ዘዴዎች የማሰራጨት፤

፪/ በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች የህይወት ዑደት ዙሪያ ዕውቀትና ክህሎትን የሚያሳድጉ ሥልጠናዎችን የመስጠት፤

፫/ በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች ብሄራዊ ተጠቃሚነትን የሚያጎለብቱ የማማከር ተግባራትን የማከናወን፤

increase the quality of innovations and researches by providing training, consulting and technical services;

2/ To establish and implement a national measurement system compatible with international standard and that enables to trace, maintain and dissiminate national measurement standards and certified reference materials to international measurement standards ;

3/ To be among the leading African institutions by making significant regional and international contributions that will ensure the sustainable benefit of our country in the fields.

6. <u>Powers and Duties</u>

The Institute shall have the following the powers and duties:

1/ Conduct scientific research in the fields of metrology and scientific equipment and disseminate research outputs through various methods;

2/ Conduct knowledge and skill enhancing training programs on metrology and Scientific Equipment life cycle;

3/ Provide Consultancy Services that could promote the benefit of the country in the areas of Metrology and Science Equipment;

፬/ ዓለም አቀፍ የአሃዶች ሥርዓት እና ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው የልኬት አሃዶች እንደ አስፈላጊነታቸው በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማስቻል፤

፭/ በብሔራዊ የሥነ-ልክ ላቦራቶሪዎች የመለኪያ ስታንዳርዶችንና የተመሰከረላቸው ማመሳከሪያ ስረቶችን የመወሰንና የመጠበቅ፤

፮/ ዓለም አቀፋዊ ስምምነት የተደረሰባቸው ሳይንሳዊ የልኬት አሃዶችን ትርጓሜ በምርምር ዕውን የማድረግ፤የተመሰከረላቸው የማመሳከሪያ ስረቶችን የማበልጸግና የማምረት፤

፯/በሥነ-ልክ ዘርፍ የምርምርና የካሊብሬሽን ላቦራቶሪዎች የማቋቋምና የማደራጀት፤

፰/በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ የምርምርና የጥገናወርክ ሾፖች የማቋቋምና የማደራጀ፤

፱/ በሥነ-ልክ ዘርፍ ለመለኪያ መሳሪያዎች ተጠቃሚ አካላት በጥናትና ምርምር የተደገፈ የካሊብሬሽን እና የቴክኒክ አገልግሎት የመስጠት፤

፲/ በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ከተቋማት አቅም በላይ ለሆኑ የሳይንስ መሣሪያዎች በጥናትና ምርምር የተደገፈ የጥገናና የቴክኒክ አገልግሎት የመስጠት፤

4/ Ensure the utilization of International System of Units and other acceptable measurement units in the country as appropriate;

5/ Determin and maintain national measurement standards and certified reference materials in national metrology laboratories;

6/ Realize Internationally agreed definitions of system of units through research, develop and produce certified reference materials;

7/ Establish and organize research and calibration laboratories in the field of metrology;

8/ Establish and organize research and scientific instrument prototype laboratories and maintenance workshops in the fields of scientific equipment;

9/ Provide research assisted calibration and technical services in the field of metrology for those who are the beneficiaries of measurement equipment;

10/ Provide research assisted maintenance and technical services in the field of scientific equipment beyond the scope of user entities for those who are the beneficiaries of scientific equipment;

CamScanner

፲፩/ በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች አገራዊ ተጠቃሚነትን ለማስፋት የካሊብሬሽን ላቦራቶሪዎችና የሳይንስ መሣሪያዎች ጥገና ወርክሾፖች ለሚያቋሙ የመንግሥትና የግል ተቋማት የቴክኒክ አገልግሎት የመስጠት፤

፲፪/ በዓለም ዓቀፍ የአሀዶች ሥርዓት ተቀባይነት ባለው ብሔራዊ የመለኪያ ስታንዳርድ ወሰን ውስጥ ለሚያርፉ የልኬት ውጤቶች ብሔራዊ የመለኪያ ስታንዳርዱ በአገሪቱ ውስጥ የመጨረሻ ትክክለኛ የልኬት መጠን ሆኖ ማገልገሉን የማረጋገጥ፤

፲፫/ የአምራችናአገልግሎት ሰጪ ኢንዱስትሪዎች ፣የምርምርና ትምህርት እንዲሁም የሌሎች የሥነ-ልክ ተጠቃሚ ተቋማት መለኪያ መሳሪያዎችን ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድት ስስር ለማስጠቅ በካሊብሬሽን የማሰራጨት፤

፲፬/ በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች የትምህርት ካሪኩለም ተቀርፆ ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ከትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር ትብብር በመፍጠር በጋራ የመስራት፤

፲፭/በሀገሪቱ ሕግ መሠረት በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች ከሌሎች አቻ ተቋማት፣ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር ዩኒቨርስቲዎችና የምርምር ተቋማት ጋር ትብብር በመፍጠር ምርምሮችንና ሌሎች

11/ Provide technical services in the fields of Metrology and Scientific equipment to governmental and private entities that have envisioned to establish calibration laboratories and scientific equipment maintenance workshops in view of enhancing country wide benefits;

12/ Ensure that the results obtained by using the national measurement standards are used as the final correct measurement results when compared with any other measurement results in the country within the calibration and measurement capability of the relevant Ethiopian metrology laboratories;

13/ Disseminate through calibration to maintain international traceability of measuring instruments used by manufacturing and service industries, research and education and other metrology users;

14/ Collaborate with educational and research institutions to develop and implement education curriculum in the fields of metrology and scientific equipment;

15/ Conduct joint researches and engage in other collaboration works with peer research institutions, regional and international institutions and local and

ስራዎችን በጋራ የመስራት፣

፲፮/ በሃገሪቱ ውስጥ በሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን የልኬት አሃዶች፣ የአሃዶቹን ምልክቶችና ብሔራዊ የመለኪያ ስታንዳርዶችን በማሳተም የማሳወቅ፤

፲፯/ ሥነ-ልክን በሚመለከት ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ ተቋማት የሚገኙ ሀገራዊ ግዴታዎችን ለመወጣትና የሚገኙ ጥቅሞችን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ምክረ ሃሳቦችን ለመንግሥት የማቅረብ፤ በመንግሥት ሲፈቀድ በዓለም አቀፍና አህጉራዊ ተቋማት ሀገሪቱን የመወከልና አባል የመሆን፣ሀገሪቱ ያፀደቀቻቸዉን ስምምነቶች ተግባራዊ የማድረግ፤

፲፰/ በብሔራዊ፣ በአህጉራዊና በዓለም አቀፍ የላቦራቶሪ የእርስ በርስ ንፅፅር ፕሮግራሞች ላይ በመሳተፍ የካሊብሬሽንና የልኬት ብቃት የማስመስከር እና በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት ተቀባይነት የማግኘት፤

፲፱/ ለብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማት መጠናከር ተገቢነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የመሥራት፤

፳/ የሥነ-ልክ እና የሳይንስ መሳሪያዎችን በተመለከተ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማደራጀት እና የማሰራጨት፤

foreign universities in the fields of metrology and scientific instruments within relevant legal frameworks of the Country,

16/ Publish and notify measurement units, symbols of units and national measurement standard to be used in the country;

17/ Submit recommendations to the government to ensure the available national benefits by fulfilling relevant regional and international responsibilities; when authorized by the government, become a member representing the country regional and international institutions; implement the agreements that the country has approved;

18/ Participate in national, regional and international inter-laboratory comparison programs to demonstrate calibration and measurement capability and get recognition by International Bureau of Weight and Measures;

19/ Collaborate with relevant stakeholders to strengthen the national quality infrastructure;

20/ Establish information and data center related to metrology and scientific

CamScanner

፳፩/ የሕጋዊሥነ-ልክ ሥርዓትን ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል አስፈላጊውን የቴክኒክና የሙያ ድጋፍ የመስጠት፤

፳፪/ በሥነ ልክና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የክፍያ ተመን የማዘጋጀት፣በሚንስትሮች ምክር ቤት በማስፀደቅ ሥራ ላይ የማዋል፡፡

፳፫/ የአገሪቱን የልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ መሰረት በማድረግ በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች የተሻሉ የፖሊሲ ሀሳቦችን በማመንጨትና ስትራቴጂዎችንና ፕሮግራሞችን በመንደፍ ለመንግስት የማቅረብ፣ሲፈቀድም ተግባራዊ የማድረግ፤

፳፬/ ዓላማውን በብቃት ሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች አካላት በውክልና የመስጠት፤

፳፭/ የንብረት ባለቤት የመሆን፣ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤

፳፮/ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

## ፯.የኢንስቲትዩቱ አቋም

ኢንስቲትዩቱ፡-

፩/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ፡ እና

equipment; organize and disseminate information;

21/ Provide the necessary technical and professional support to make the legal metrology system effective;

22/ Drafts a fee structure for the services it provides and implements it on approval by the Council of Ministers.

23/ Propose better policy ideas, design strategies and programs in the fields of metrology and scientific equipment based on national development policy and strategy, and submit to the Ministry and implement same upon approval by the Ministry;

24/ Delegate part of its powers and duties to other organs when it finds necessary for the effective implementation of its objectives;

25/ Own property, inter into contract, sue and be sued in its own name;

26/ Carry out other related activities necessary for the achievement of its objectives.

## 7. Organization of the Institute

The Institute shall have:

1/ A Director General and, as required Deputy Director Generals to be appointed by the country's Prime Minister; and

Magenta Yellow Black

CamScanner

፪/ አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

፰.የዋና ዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተዘረዘሩትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ)የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን እና መሠረታዊ መርሆዎችን ተከትሎ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፤

ሐ)የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራም እና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው የሥራ ፕሮግራምና በጀት መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ)ኢንስቲትዩቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ)የኢንስቲትዩቱን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

2/ the necessary staff.

8. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Institute and shall direct and administer the activities of the Institute.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) Exercise the powers and duties of the Institute specified under Article 6 of this Regulation;

b) Employ and administer employees of the Institute in accordance with the Federal Civil Service Law and its basic principles;

c) Prepares the Institute's strategic and annual plans, work programs and budgets and submits to the Ministry and implement same upon approval by the Ministry;

d) Effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Institute;

e) Represent the Institute in its dealings with third parties;

f) Prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute.

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፱.የምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተሩ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የተመደበበትን ዘርፍ ሥራ ያቅዳል፤ ያስተባብራል፣ ይመራል፤

፪/ በዋና ዳይሬክተሩ ተለይተዉ የሚሰጡን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል፤ ከአንድ በላይ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ካሉና ዋና ዳይሬክተሩ በተለይ ካልወከለ በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶት ይሠራል።

**፲.በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

**፲፩.የሂሣብ መዛግብት**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፡፡

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and staff of the Institute to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Institute.

**9.Powers and Duties of Deputy Director General**

Deputy Director General, being accountable to the Director General shall have the following Powers and Duties:

1/ Plans, coordinates and directs the functions entrusted to the sector he is assigned to;

2/ Performs other duties assigned by the Director General;

3/ In the absence of the Director General, the Deputy Director General shall, act on his behalf; where there are more than one Deputy Director Generals and no specific delegation has been given by the Director General, the Deputy Director General who is senior by appointment shall act on behalf of the Director General.

**10.Budget**

The budget of the Institute shall be allocated by the government.

**11.Book of Accounts**

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

፪/የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ፲፪.የተሻረ ደንብ

የብሔራዊ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፬/፪ሺ፲ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

## ፲፫.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡

## ፲፬.መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ

የብሔራዊ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል፡፡

## ፲፭.ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

ዶ/ር አብይ አህመድ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

2/ The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or an auditor assigned by him.

## 12.Repealed Regulation

National Metrology Institute Establishment Council of MinistersRegulation No.194/2010 is hereby repealed by this Regulation.

## 13.Inapplicable Laws

Any regulation, directive or practice inconsistent with this Regulation shall not be applied to matters covered by this Regulation.

## 14.Transfer of the Rights and Obligations

The Rights and Obligations of the National Metrology Institute are transferred to the Ethiopian Metrology Institute established by this Regulation.

## 15.Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Addis Ababa the 30th day of July,2024

ABIY AHMED (PhD)

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA